አሰቀድመው ያንብቡ

ብፁዕ*
Garland F. Byers, Jr., J.D., D.D.‡
የእሕዛብ ጳጳስ፣ በሐዋርያዊ ተልእኮ

✠

የጳጳሱን በቁጥር የተሰየሙ የትምህርተ ሃይማኖት መግለጫዎች የሚያነቡ ከሆነ፣ ያለ ምንም እንቅፋትና ያለ ምንም መሰናክል ያነቡ ዘንድ ይህን ጸሎት እንዲጸልዩ፣ በሁለተኛው ክፍል ያለውንም የማሰር ክፍል አንብበው በእርሱ እንዲሰማሙ በብርቱ ይመክራል።

✠

ክፍል አንድ፦ የማሰር ጸሎት

ይህ ጸሎት ከሁለት ክፍሎች የመጀመሪያው እንዲሆን የታሰበ ነው፤ ዓላማውም ስለ መንፈሳዊ ውጊያ ጉዳዮች የሚናገርን ሐዋርያዊ ጽሑፍ በሚያነብበት ጊዜ ለአንባቢው ተገቢውን መንፈሳዊ የአእምሮ ዝግጅትና መንፈሳዊ ጥበቃ መሰጠት ነው። ይህ የማሰር ጸሎት ከእርሱ ቀጥሎ ካለው የማሰር ሐዋርያዊ ትእዛዝ ጋር አብሮ እንዲነበብ የታሰበ ነው። ጸሎቱ እግዚአብሔር ማሰሩን በራሱ እንዲያጸናው ይለምናል፤ ከዚያም ጳጳሱ ሐዋርያዊ የማሰር ትእዛዝ ይሰጣሉ፤ እግዚአብሔርም ይህን ትእዛዝ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲያሰፈጽመው ይለመናል።[1]

ሁሉን የምትችል[2] ልዑል እግዚአብሔር ሆይ፣[3] በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣[4] የሰማይና የምድር ፈጣሪ ሆይ፣[5] እኛ[6] በጸሎት ወደ አንተ እንቀርባለን፤[7] የምንቀርበውም በስም ነው፤[8] ይኸውም በአንድያ ልጅህ፣[9] በኢየሱስ፣[10] በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ባለው በአንዱ መካከለኛ ስም ነው።[11] አባት ሆይ፣ እነዚህ ጽሑፎች የቃልህ ሐዋርያዊ ትምህርቶች ናቸው፤[12] አንተንና ልጅህን ኢየሱስ ክርስቶስን ያከብሩ ዘንድም የታሰቡ ናቸው።[13] ጠላት[14] ቃሉ እንደ ተዘራ ወዲያው እንደሚመጣ፣[15] ሰዎችም አምነው እንዳይድኑ ቃሉን ከልብ እንደሚወስደው እናውቃለን።[16] ሰይጣን እስከ ክርስቶስ መመለስ ድረስ የዚህ ዓለም አምላክ ነው፤[17] የሰዎችንም አእምሮ ያሳውራል፤[18] መሰማትን ያደነዝዛል፤[19] ሁከትን ይፈጥራል፤[20] አማኙም የተማረውን እንዲረሳ ያደርጋል።[21]

ስለዚህ፣ አባት ሆይ፣ የሚከተለውን እንለምናለን፤ [22] የምንለምነውም እነዚህን ሐዋርያዊ ጽሑፎች ለሚያነቡ ሁሉ ነው፦ [23]

መንፈሰ ቅዱሰ ኃይልን ይሰጣቸው ዘንድ እንለምናለን፤ [24] ይኸውም እነዚህን ትምህርቶች በማስተዋል [25] በመለየትም ያነቡ ዘንድ፣ [26] በክርስቶስ ልብ ያነቡ ዘንድ፣ [27] በሥጋዊና በወደቀ አእምሮም እንዳያነቡ ነው። [28]

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የላከው መንፈሰ ቅዱስ፣ [29] ጌታ ወደ ቀኛህ ባረገ ጊዜ የላከው፣ [30] በመንፈሳዊ ዓይኖች ያነቡ ዘንድ እንዲፈቅድላቸው፣ [31] ሁሉንም ነገር እንዲያሳስባቸውም እንለምናለን። [32]

ልባቸው ተግሣጽን ለመቀበል እንዲከፈት፣ [33] ወደ እውነትም ሁሉ እንዲመሩ፣ [34] እነዚህን ትምህርቶች በማንበባቸውም ወደ አንተ ይበልጥ እንድታቀርባቸው፣ [35] በእውነትህም እንዲቀደሱ እንለምናለን። [36]

ክፉውን እንድታሰረው እንለምናለን፤ [37] እርሱ የሐሰት አባት ነው፤ [38] የሰው ልጅ ጠላት ነው፤ [39] አንተንና እኛን ይጠላል፤ [40] እኛም በመልክህ የተፈጠርን ነን። [41] ማስተዋልን እንዳይከለክል፣ [42] እውነትን በመሰማታቸው ምክንያት ስሜቶቻቸውን በክፉ እንዳያነሣሣ፣ [43] ጆሮአቸውን እንዳይደፍንና ልባቸውን እንዳያደነድን፣ [44] እነዚህንም ትምህርቶች እንዲረሱ እንዳያደርግ፣ [45] በዚህም ትምህርቶቹን በእነርሱ ዘንድ ፍሬ አልባ እንዳያደርግ፣ [46] አሁን ባለንበት በዚህ መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ እንድታሰረው እንለምናለን። [47]

እነዚህን ትምህርቶች የሚያነቡትን እንድትባርክ እንጸልያለን፤ [48] እነርሱንና ቤታቸውን ባርክ፤ [49] ጠላትም አጸፋ እንዳይመልሰባቸው አሰረው፤ [50] አጸፋውም ፊትህን ስለ ፈለጉ ነውና። [51] የኢየሱስ ደም በእነርሱ ላይ እንዲሆን እንጸልያለን፤ [52] በእነዚህ ትምህርቶችና በመላው መንፈሳዊ ቤታቸውም ላይ። [53] አቤቱ፥ ኃይልህን ግለጥ፤ [54] የቀባኸውንም ጠብቅ። [55]

እነዚህ ትምህርቶች አንባቢዎቹን እንዲያዘጋጁ እንለምናለን፤ [56] በአንተ ዘንድ ደስ የሚያሰኝ የጽድቅ ሕይወት እንዲኖሩ፣ [57] ክርስቶስንም ይበልጥ እየመሰሉ እንዲያድጉ፣ [58] ይህም ዕለት ዕለት እንዲሆን። [59]

በመጨረሻም፣ አባት ሆይ፣ መንፈሳዊውን ማስር እንድታጸናው እንለምናለን፤ [60] ይኸውም ባሪያህ አሁን በእነዚህ ጽሑፎች ላይ የሚያደርገው ማስር ነው፤ [61] ጠላትም እንዲሸሽ፣ [62] ጠላትም በፍርሃት እንዲንቀጠቀጥ እንለምናለን፤ [63] ይህም የጥበቃህን አጥር ቢተላለፉ ነው። [64]

ምስጋናና ውዳሴ እናቀርብልሃለን፤ [65] አባት ሆይ፣ በዚህ መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ያለ መከላከያ ሰላልተውኸን። [66] ቃልህን ሰጥተኸናል፤ እርሱም የመንፈሰ ሰይፍ ነው፤ [67] ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅም የተሳለ ነው። [68] የዘላለም ሕይወት ይኖረን ዘንድ አንድያ ልጅህን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፈህ ሰጥተሃል፤ [69] ይህም በሽንፈት ሳይሆን ከድል ሰፍራ ሆነን እንድንዋጋ ነው፤ [70] ክርስቶስ አለቅነትንና ሥልጣናትን ድል ነሥቶ አሳፍሮአቸዋልና፤ [71] እነዚህም በዚህ ዓለም አምላክ በከፍተኛ ሰፍራ የተሾሙ ናቸው። [72] በደሙ ተፈውሰናል፤ [73]

ከአንተ ጋር ታርቀናል፤[74] የድልንና የዘላለም ሕይወትን አክሊል ተቀብለናል።[75] ወደ እውነት ሁሉ ይመራን ዘንድ መንፈስ ቅዱስህን ልከሃል፤[76] በምድር ላይ ያለውን የክርስቶስን አካል፣ ቤተ ክርስቲያንን፣ ሰጥተኸናል፤[77] ስለ እርሷም ክርስቶስ እንዲህ አለ፦ «...የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።»[78]

አባት ሆይ፣ ስለ ስማኽንም እናመሰግንሃለን፤[79] እንድትባርከንና ጸሎታችንን እንድትመልስልን በእምነት እናውቃለን።[80]

ይህን ሁሉ በሰሙ እንለምናለን፤[81] በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም።[82] አሜን።[83]

> **ልብ ይበሉ፦** የማሰር ጸሎቱ ብቻውን ሲቆም ውጤት አልባ ሊሆን ይችላል። ጸሎቱ ራሱ እንደሚያመለክተው፣ ሰይጣንና ከሃዲ ሠራዊቱ አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል በሚያነቡ ሰዎች ላይ ይነሣሉ፤ አጸፋም ይመልሱባቸዋል። ጳጳሱ ይህን እጅግ ከባድ ጉዳይ፣ የሚቻለውን ሙሉ ጥበቃ የሚጠይቅ ጉዳይ አድርገው ይመለከቱታል። ስለዚህ አንባቢው የማሰር ሐዋርያዊ ትእዛዝንም እንዲያነብ፣ በጸሎትም መንፈስ እንዲያነበው ይበረታታል።

አንባቢው በዚህ ድረ ገጽ ላይ የሚገኙትን ሐዋርያዊ ጽሑፎች በሚያነብበት ጊዜ ሙሉ ጥበቃ እንዲያገኝ፣ አሁን በአክብሮትና በጸሎት ወደ የማሰር ሐዋርያዊ ትእዛዝ ይመራል።

✠

ክፍል ሁለት፦ የማሰር ሐዋርያዊ ትእዛዝ

የማሰር ሐዋርያዊ ትእዛዝ በመዘጋጀት ላይ ሲሆን እዚህ ይታተማል። በዚህ ድረ ገጽ ላይ ያሉትን ሐዋርያዊ ጽሑፎች ከማንበብ በፊት ከማሰር ጸሎቱ ጋር አብሮ ይነበባል።

ለመጨረሻ ጊዜ የተከለሰው፦ ኦክቶበር *19* ቀን *2026* እ.ኤ.አ

✠

ማስታወሻዎች

1 ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ሺህ ዓመታት ያህል፣ ሰይጣንና ከሃዲ ሠራዊቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ እውነትን እንዳያውቁ ለማድረግ በማቀድ የእግዚአብሔርን ቃል በልዩ ልዩ መንገድ ከእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሚሰርቁ ሰታውቅ መኖሯ ለእኔ ታላቅ ምሥጢር ነው። «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።» የዮሐንስ ወንጌል 14:6 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። ሆኖም እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ የትኛውም የቤተ ክርስቲያን ጽሑፍ ወይም የየትኛውም ክርስቲያን ደራሲ ጽሑፍ በማሰር ጸሎት ወይም የጳጳስነትን ወይም የሐዋርያነትን ሥልጣን በያዘ ሰው በሚሰጥ የማሰር ትእዛዝ አይጀምርም። ቤተ ክርስቲያንና የክርስቶስ አካል ብልቶች አሁን ያሉበት መንፈሳዊ ውጊያ የታወቀ ከመሆኑ አንጻር፣

ስለ ክርስትና እምነት ጉዳዮች በሚናገሩ ጽሑፎች ሁሉ እንዲህ ያለውን የማስር ጸሎት ማካተት ምክንያታዊና ጥበብ ያለበት ሆኖ ይታየኛል።

2 «...እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለትና። እኔ ኤልሻዳይ ነኝ፤ በፊቴ ተመላለስ፥ ፍጹምም ሁን» ኦሪት ዘፍጥረት 17:1 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የነበረውና ያለ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም።» የዮሐንስ ራእይ 4:8 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

3 «የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ፤ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ። ባረከውም። አብራም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው፤» ኦሪት ዘፍጥረት 14:18-19 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ወደሚረዳኝ እግዚአብሔር ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጮኻለሁ።» መዝሙረ ዳዊት 57:2 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

4 «እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ። በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥ ስምህ ይቀደስ...» የማቴዎስ ወንጌል 6:9-10 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

5 «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።» ኦሪት ዘፍጥረት 1:1 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፥ አይታክትም...» ትንቢተ ኢሳይያስ 40:28 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።» መዝሙረ ዳዊት 121:2 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ጌታ ሆይ፥ አንተ ሰማዩንና ምድሩን ባሕሩንም በእነርሱም የሚኖረውን ሁሉ የፈጠርህ፥» የሐዋርያት ሥራ 4:24 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

6 እዚህ ላይ «እኛ» የሚለው ቃል ጸሐፊውን ጳጳስ ብቻ ሳይሆን አንባቢውንም ያመለክታል።

7 «እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።» ወደ ዕብራውያን 4:16 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

8 «...አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል።» የዮሐንስ ወንጌል 16:23 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ።» የዮሐንስ ወንጌል 14:13 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

9 «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።» የዮሐንስ ወንጌል 3:16 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።» የዮሐንስ ወንጌል 1:18 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና።» 1ኛ የዮሐንስ መልእክት 4:9 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

10 «...እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።» የማቴዎስ ወንጌል 1:21 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

11 «አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤» 1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:5 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።» የዮሐንስ ወንጌል 14:6 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...በሚሻል ተስፋ ቃል በተመሠረተ በሚሻል ኪዳን ደግሞ መካከለኛ እንደሚሆን...» ወደ ዕብራውያን 8:6 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። ቅዱሳት መጻሕፍት ሳይጓደሉ እንዲጠቀሱ፣ «በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል» የሚለው አገላለጽ ከመጀመሪያው ግሪክኛ እንደ ተተረጎመው በ1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:5 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) እንደ ተመዘገበው ተጠብቋል። የግሪክኛው ቃል *anthrōpos* (Strong's G444) ነው፤ ይህም ወንድ የሆነውን ሰው ከሚያመለክተው *anēr* (G435) በተለየ፣ ጾታን ሳይለይ የሰው ልጆችን ያመለክታል።

ስለዚህ ጥቅሱ ሴቶችንና ወንዶችን በእኩል ያጠቃልላል፤ በክርስቶስ ዘንድ «ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።» ወደ ገላትያ ሰዎች 3:28 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

12 «በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።» የሐዋርያት ሥራ 2:42 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እንግዲያስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጸንታችሁ ቁሙ፥ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ።» 2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2:15 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:20 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ቃሉን ስበክ፥ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፥ ዝለፍና ገሥጽ ምክርም።» 2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 4:2 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

13 «ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር...ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ፤ አሜን።» 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 4:11 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «አባት ሆይ፥ ሰዓቱ ደርሶአል፤ ልጅህ ያከብርህ ዘንድ...ልጅህን አክብረው።» የዮሐንስ ወንጌል 17:1 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ...» የዮሐንስ ወንጌል 5:22-23 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።» 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 10:31 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

14 «በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤» 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 5:8 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

15 «በስሙት ጊዜም ሰይጣን ወዲያው መጥቶ በልባቸው የተዘራውን ቃል ይወስዳል።» የማርቆስ ወንጌል 4:15 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ክፉው ይመጣል፥ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል» የማቴዎስ ወንጌል 13:19 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

16 «በመንገድ ዳርም ያሉት የሚሰሙ ናቸው፤ ከዚህ በኋላም ዲያብሎስ ይመጣል አምነውም እንዳይድኑ ቃሉን ከልባቸው ይወስዳል።» የሉቃስ ወንጌል 8:12 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

17 «...አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል» የዮሐንስ ወንጌል 12:31 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...በማይታዘዙትም ልጆች ላይ አሁን ለሚሠራው መንፈስ አለቃ እንደ ሆነው በአየር ላይ ሥልጣን እንዳለው አለቃ...» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 2:1-2 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።» 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 4:4 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ያሳታቸውም ዲያብሎስ እውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ።» የዮሐንስ ራእይ 20:10 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

18 «ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።» 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 4:4 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

19 «አንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ፥ እኔ አዝሃለሁ፥ ከእርሱ ውጣ እንግዲህም አትግባበት» የማርቆስ ወንጌል 9:25 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፥ ክፉው ይመጣል፥ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል» የማቴዎስ ወንጌል 13:19 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

20 «እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ የሁከት አምላክ አይደለምና፤ በቅዱሳንም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንዲህ ነው።» 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 14:33 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም፤ ነገር ግን የምድር ነው፥ የሥጋም ነው፥ የአጋንንትም ነው፤ ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ሰፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሰራ ሁሉ አሉና።» የያዕቆብ

መልእክት 3:15-16 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ።» 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 11:3 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

21 «ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ፥ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያሰፈልገናል።» ወደ ዕብራውያን 2:1 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ምንም ብታውቁ በእናንተም ዘንድ ባለ እውነት ምንም ብትጸኑ፥ ስለ እነዚህ ዘወትር እንዳሳሰባችሁ ቸል አልልም።» 2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:12 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ቃልም በተዘራበት በመንገድ ዳር የሆኑት እነዚህ ናቸው፥ በሰሙት ጊዜም ሰይጣን ወዲያው መጥቶ በልባቸው የተዘራውን ቃል ይወስዳል።» የማርቆስ ወንጌል 4:14-15 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

22 «...በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።» ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 4:6 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል።» የማቴዎስ ወንጌል 7:7 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

23 «ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም።» ወደ ቆላስይስ ሰዎች 1:9 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ስለ እናንተ እያመሰገንሁ ሰጸልይ ስለ እናንተ ማሳሰብን አልተውም፤ የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ።» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:16-17 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

24 «ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ...» የሐዋርያት ሥራ 1:8 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «በመንፈሱ በውስጥ ሰውነታችሁ በኃይል እንድትጠነክሩ...እንደ ክብሩ ባለ ጠግነት መጠን ይሰጣችሁ...» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 3:16 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

25 «የምለውን ተመልከት፤ ጌታም በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይስጥህ።» 2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:7 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤» የሉቃስ ወንጌል 24:45 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

26 «እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና። ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።» የሐዋርያት ሥራ 17:11 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤» 1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 5:20-21 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በሰራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው...» ወደ ዕብራውያን 5:14 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...የሚሻለውን ነገር ፈትናችሁ ትወዱ ዘንድ፥ ፍቅራችሁ በእውቀትና በማስተዋል ሁሉ ከፊት ይልቅ እያደገ እንዲበዛ ይህን እጸልያለሁ።» ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 1:9-10 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

27 «እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።» 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2:16 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።» ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 2:5 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

28 «ስለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ ግን ሕይወትና ሰላም ነው። ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተሰኖታል፤» ወደ ሮሜ ሰዎች 8:6-7 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም የሚመረመር ስለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም።» 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 2:14 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...እሕዛብ ደግሞ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትመላለሱ...እነርሱ ባለማወቃቸው ጠንቅ በልባቸውም ደንዳንነት ጠንቅ

ልቡናቸው ጨለመ፥ ከእግዚአብሔርም ሕይወት ራቁ፤» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:17-18 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት...» ወደ ሮሜ ሰዎች 5:12 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

29 «እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ።» የዮሐንስ ወንጌል 16:7 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤» የዮሐንስ ወንጌል 15:26 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

30 «ስለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው።» የሐዋርያት ሥራ 2:33 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ።» የማርቆስ ወንጌል 16:19 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

31 «ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን...» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:18 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ዓይኖቼን ክፈት፥ ከሕግህም ተኣምራትህን አያለሁ።» መዝሙረ ዳዊት 119:18 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ኤልሳዕም። አቤቱ፥ ያይ ዘንድ ዓይኖቹን፥ እባክህ፥ ግለጥ ብሎ ጸለየ...» 2ኛ መጽሐፈ ነገሥት 6:17 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

32 «አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።» የዮሐንስ ወንጌል 14:26 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

33 «...ልድያ የሚሉአት...ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት።» የሐዋርያት ሥራ 16:14 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ልብህን ለተግሣጽ ስጥ፥ ጆሮህንም ወደ እውቀት ቃል።» መጽሐፈ ምሳሌ 23:12 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን በውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በየዋህነት ተቀበሉ።» የያዕቆብ መልእክት 1:21 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

34 «ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል...» የዮሐንስ ወንጌል 16:13 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

35 «የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም...» የዮሐንስ ወንጌል 6:44 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «... በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ፤ ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ።» ትንቢተ ኤርምያስ 31:3 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል» የያዕቆብ መልእክት 4:8 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምር ከሥርዓቴ ፈቀቅ ብላችኋል፥ እርሰዋንም አልጠበቃችሁም። ወደ እኔ ተመለሱ፥ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።» ትንቢተ ሚልክያስ 3:7 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ስለዚህ እንዲህ በላቸው። የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ወደ እኔ ተመለሱ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር።» ትንቢተ ዘካርያስ 1:3 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

36 «በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው።» የዮሐንስ ወንጌል 17:17 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኋልና፤» 2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2:13 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

37 «ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም።» የዮሐንስ ወንጌል 17:15 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፥ ሺህ ዓመትም አሰረው...» የዮሐንስ ራእይ 20:1-3 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ እቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል?»

የማቴዎስ ወንጌል 12:29 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ነገር ግን የሚያጸናችሁ ከክፉውም የሚጠብቃችሁ ጌታ የታመነ ነው።» 2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 3:3 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

38 «እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።» የዮሐንስ ወንጌል 8:44 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

39 «...የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው...» የማቴዎስ ወንጌል 13:39 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤» 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 5:8 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ...» የሉቃስ ወንጌል 10:19 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

40 «...ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፥ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና።» የዮሐንስ ራእይ 12:12 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ፤» የዮሐንስ ራእይ 12:17 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበረ» የዮሐንስ ወንጌል 8:44 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

41 «እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።» ኦሪት ዘፍጥረት 1:27 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። “For God created man to be immortal, and made him to be an image of his own eternity. Nevertheless through envy of the devil came death into the world . . .” መጽሐፈ ጥበብ 2:23-24 (KJV) (ይህ መጽሐፍ በ1954 ዓ.ም. ትርጉም ውስጥ የለም)።

42 «የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፥ ክፉው ይመጣል፥ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል» የማቴዎስ ወንጌል 13:19 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።» 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 4:4 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

43 «ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:26-27 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ይህንም በሰሙ ጊዜ በልባቸው በጣም ተቈጡ ጥርሳቸውንም አፋጩበት።» (ለእስጢፋኖስ ሰብከት የተሰጠ ምላሽ) የሐዋርያት ሥራ 7:54 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እንኪያስ እውነቱን ስለ ነገርኋችሁ ጠላት ሆንሁባችሁን?» ወደ ገላትያ ሰዎች 4:16 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ሰው ሁሉ ለመሰማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፤ የሰው ቍጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና።» የያዕቆብ መልእክት 1:19-20 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

44 «...የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአልና ጆሮአቸውም ደንቁሮአል ዓይናቸውንም ጨፍነዋል...» የማቴዎስ ወንጌል 13:15 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ነገር ግን ከእናንተ ማንም በኃጢአት መታለል እልከኛ እንዳይሆን፥ ዛሬ ተብሎ ሲጠራ ሳለ፥ በእያንዳንዱ ቀን እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ፤» ወደ ዕብራውያን 3:13 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮአችሁም ያልተገረዘ፥ እናንተ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ...» የሐዋርያት ሥራ 7:51 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

45 «በሰሙት ጊዜም ሰይጣን ወዲያው መጥቶ በልባቸው የተዘራውን ቃል ይወስዳል።» የማርቆስ ወንጌል 4:15 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው፥ በሥራው የተባረከ ይሆናል።» የያዕቆብ መልእክት 1:25 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ምናልባት እንዳንወሰድ...» ወደ ዕብራውያን 2:1 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

46 «...የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል፥ የማያፈራም ይሆናል።» የማቴዎስ ወንጌል 13:22 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ባስተላለፋችሁትም ወግ የእግዚአብሔርን ቃል ትሽራላችሁ...» የማርቆስ ወንጌል 7:13 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

47 «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ሰፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6:12 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን፥ እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፥» 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 10:3-5 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6:17 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

48 «...የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።» የዮሐንስ ራእይ 1:3 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እግዚአብሔር ይባርክህ፥ ይጠብቅህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ፥ ይራራልህም፤ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ያንሣ፥ ሰላምንም ይስጥህ።» ኦሪት ዘኍልቍ 6:24-26 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

49 «...አሁን እንግዲህ ለዘላለም በፊትህ ይሆን ዘንድ የባሪያህን ቤት፥ እባክህ፥ ባርክ...» 2ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 7:29 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) (ዳዊት በመንፈሳዊ ቤቱ ላይ በረከትን ሲለምን፤ ለዚህ ጸሎት ቀጥተኛ አብነት ነው)። «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ» የሐዋርያት ሥራ 16:31 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

50 «እርሱንና ቤቱን በዙሪያውም ያሉትን ሁሉ አላጠርህለትምን?...» መጽሐፈ ኢዮብ 1:10 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) (የእግዚአብሔር ጥበቃ በጻድቃንና በቤታቸው ዙሪያ እንደ አጥር ሆኖ እንደሚያገለግል የሚያሰረዳው የተመዘገበው የሰይጣን ቃል [ይህም የኢዮብን መጽሐፍና ከዚያም ባሻገር ያለውን በዝርዝር በመመርመር የተረጋገጠ ሲሆን ከዚህ ጥቅስ ወሰን ውጭ ነው]። አብሬአቸው ያገለገልኋቸውን ክርስቲያን ምእመናን በምረዳበት ጊዜ ይህን «አጥሩን መጸለይ» ብዬ ጠርቼዋለሁ)። «ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ...» የሉቃስ ወንጌል 22:31-32 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ኋላም በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላሉ።» የማርቆስ ወንጌል 4:17 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) (ይህ ጥቅስ ሰይጣንና ከሃዲ ሠራዊቱ የእግዚአብሔርን ቃል ሰሚ ወይም አነባቢ ቃሉን ሰለ ተቀበለ አጸፋ ሊመልሱበት እንደሚችሉ፣ አንዳንድ ጊዜም እንደሚመልሱበት ያሳያል። ይህ ጸሎት እግዚአብሔር በዚህ ትምህርት ይህን እንዳይፈቅድ ይለምናል)። «ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፥ መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም።» መዝሙረ ዳዊት 91:10 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) (... በጸሎት ሰለ ተለመነው፣ እግዚአብሔርም ሰለ ሰማውና ሰለ መለሰው አጥር)።

51 «አንተ ፊቴን እሹት ባልህ ጊዜ። አቤቱ፥ ፊትህን እሻለሁ ልቤ አንተን አለ።» መዝሙረ ዳዊት 27:8 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) (እግዚአብሔር ፊቱን እንድንፈልግ የሰጠው ቀጥተኛ ትእዛዝ፣ እዚህም የተቀበልነው)። «በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈግሉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ...» 2ኛ መጽሐፈ ዜና መዋዕል 7:14 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

52 «ደሙም ባላችሁበት ቤቶች ምልክት ይሆንላችኋል፤ ደሙንም ባየሁ ጊዜ ከእናንተ አልፋለሁ...መቅሰፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም።» ኦሪት ዘጸአት 12:13 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና፤» 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 5:7 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት...» የዮሐንስ ራእይ 12:11 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...በመንፈስም እንደሚቀደሱ፥ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ...» 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:1-2 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

53 «እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።» 1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 2:5 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እነዲሁም በድንኳኒቱና በማገልገያው ዕቃ ሁሉ ደምን ረጨ። እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል...» ወደ ዕብራውያን 9:21-22 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) (እዚህ ደም በአገልግሎት ለሚውሉ ነገሮች ይደረጋል፤ የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ደግሞ፣ በእርግጥ፣ ዋናው መሣሪያ ነው)።

54 «እግዚአብሔር ይነሣ፥ ጠላቶቹም ይበተኑ፥ የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ።» መዝሙረ ዳዊት 68:1 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «የእግዚአብሔር ክንድ ሆይ፥ ተነሥ፥ ተነሥ፥ ኃይልንም ልበስ፤ በቀድሞው ወራትና በጥንቱ ዘመን በነበረው ትውልድ እንደ ሆነው ተነሥ...» ትንቢተ ኢሳይያስ 51:9 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «አቤቱ፥ በኃይልህ ከፍ ከፍ በል፤ ድናትህንም እናመሰግናለን እንዘምርማለን።» መዝሙረ ዳዊት 21:13 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ለምናምን ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን...» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:18-19 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

55 «አቤቱ፥ መታመናችንን እይልን፥ ወደ ቀባኸውም ፊት ተመልከት።» መዝሙረ ዳዊት 84:9 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «የቀባኋቸውን አትዳሰሱ፥ በነቢያቴም ክፉ አታድርጉ...» መዝሙረ ዳዊት 105:14-15 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እግዚአብሔር ለሕዝቡ ኃይላቸው ነው፥ ለቀባውም የመድኃኒቱ መታመኛ ነው።» መዝሙረ ዳዊት 28:8 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፥ ሁሉንም ታውቃላችሁ።» 1ኛ የዮሐንስ መልእክት 2:20 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) (አማኞች ሁሉ የተቀቡ ናቸው)።

56 «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» 2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3:16-17 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ...ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:11-12 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእናንተ እያደረገ፥ ፈቃዱን ታደርጉ ዘንድ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹማን ያድርጋችሁ...» ወደ ዕብራውያን 13:21 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

57 «...እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር...በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።» 1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:1-3 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።» ወደ ሮሜ ሰዎች 12:1-2 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር...» ወደ ቲቶ 2:12 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

58 «እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመሰል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።» 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 3:18 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:15 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ...» 2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 3:18 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «የጻድቃን መንገድ ግን እንደ ንጋት ብርሃን ነው፥ ሙሉ ቀን እስኪሆንም ድረስ እየተጨመረ ይበራል።» መጽሐፈ ምሳሌ 4:18 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

59 «...የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል።» 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 4:16 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

60 «የባሪያዬን ቃል አጸናለሁ፥ የመልእክተኞቼንም ምክር እፈጽማለሁ...» ትንቢተ ኢሳይያስ 44:26 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) (እግዚአብሔር ባሪያው የሚናገረውን ቃል እንዲያጸናውና እንዲፈጽመው መለመን)። «እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታሰሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል...ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢሰማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል።» የማቴዎስ ወንጌል 18:18-19 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፥ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፥ በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር።» የማርቆስ ወንጌል 16:20 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

61 «ሐዋርያ ሊሆን የተጠራ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ጳውሎስ...ለእግዚአብሔር ወንጌል ተለየ።» ወደ ሮሜ ሰዎች 1:1 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደ ሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና፥ ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን።» 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 4:5 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታሰረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል...» የማቴዎስ ወንጌል 16:19 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

62 «እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤» የያዕቆብ መልእክት 4:7 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ከእናንተም አምስቱ መቶውን ያሳድዳሉ፥ መቶውም አሥሩን ሺህ ያሳድዳሉ፤ ጠላቶቻችሁም በፊታችሁ በሰይፍ ይወድቃሉ።» ኦሪት ዘሌዋውያን 26:8 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እግዚአብሔርም በላይህ የሚቆሙትን ጠላቶችህን በፊትህ የተመቱ ያደርጋቸዋል፤ በአንድ መንገድ ይመጡብሃል፥ በሰባትም መንገድ ከፊትህ ይሸሻሉ።» ኦሪት ዘዳግም 28:7 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እግዚአብሔር ይነሣ፥ ጠላቶቹም ይበተኑ፥ የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ።» መዝሙረ ዳዊት 68:1 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

63 «እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።» የያዕቆብ መልእክት 2:19 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ፍርሃትና ድንጋጤ ወደቀባቸው፤ በክንድህ ብርታት እንደ ድንጋይ ዝም አሉ።» ኦሪት ዘጸአት 15:16 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...ጊዜው ሳይደርስ ልትሣቀየን ወደዚህ መጣህን?» የማቴዎስ ወንጌል 8:29 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) (ይህ በጠላት ዘንድ ያለውን እግዚአብሔርን መፍራት የሚያሳይ ምሳሌ ነው፤ በክርስቶስ ያሉ ምእመናንም በኃይሉ ደግሞ ያምኑ ዘንድ ተመዝግቧል)።

64 «እርሱንና ቤቱን በዙሪያውም ያሉትን ሁሉ አላጠርህለትምን?...» መጽሐፈ ኢዮብ 1:10 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) (ሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር፣ እግዚአብሔር ከኢዮብ ጋር በማንኛውም መንገድ የተያያዘውን ማንኛውንም ነገር እንዳይነካ እንደ ከለከለው ሲያምን፤ ይህም በኢዮብና ከእርሱ ጋር በተያያዘው ሁሉ ዙሪያ የጥበቃ አጥር፣ የቅዱስ እሳት አጥር፣ የተደረገ ያህል ነበር) («አጥር» ሰይጣን ራሱ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ጥበቃ ለመግለጽ እንደ ተጠቀመበት ቅዱሳት መጻሕፍት የመዘገቡት ቃል ራሱ ነው)። «እኔ በዙሪያዋ የእሳት ቅጥር እሆንላታለሁ፥ በውስጥዋም ክብርን እሆናለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር።» ትንቢተ ዘካርያስ 2:5 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፥ ያድናቸውማል።» መዝሙረ ዳዊት 34:7 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና፤» መዝሙረ ዳዊት 91:11 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

65 «ወደ ደጆቹ በመገዛት፥ ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ፤ አመስግኑት፥ ስሙንም ባርኩ፤» መዝሙረ ዳዊት 100:4 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።» ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 4:6 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

66 «ወላጆች እንደ ሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ።» የዮሐንስ ወንጌል 14:18 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6:11 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤» 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 10:4 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

67 «የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6:17 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

68 «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ሰሜትና አሳብ ይመረምራል፤» ወደ ዕብራውያን 4:12 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

69 «ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ስለ ሁላችን አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?» ወደ ሮሜ ሰዎች 8:32 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር እንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።» የዮሐንስ ወንጌል 3:16 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

70 «ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።» 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 15:57 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን።» ወደ ሮሜ ሰዎች 8:37 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።» 1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5:4 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

71 «አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ ድል በመንሣት በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው።» ወደ ቆላስይስ ሰዎች 2:15 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

72 «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ሰፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 6:12 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።» 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 4:4 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

73 «እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ በደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍሰል እኛ ተፈወስን።» ትንቢተ ኢሳይያስ 53:5 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ሰርየት።» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:7 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

74 «ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤» ወደ ሮሜ ሰዎች 5:10 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ...» ወደ ቆላስይስ ሰዎች 1:19-20 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

75 «በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተሰፋ ሰለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።» የያዕቆብ መልእክት 1:12 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «...እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።» የዮሐንስ ራእይ 2:10 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

76 «ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል...» የዮሐንስ ወንጌል 16:13 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

77 «እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ።» 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 12:27 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው። እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ ሙላቱ ናት።» ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:22-23 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

78 «እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።» የማቴዎስ ወንጌል 16:18 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

79 «አባት ሆይ፥ ሰለ ስማኸኝ አመሰግንሃለሁ።» የዮሐንስ ወንጌል 11:41 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም) (አልዓዛር ከመነሣቱ በፊት ክርስቶስ ሲያመሰግን)። «በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ ፈቃዱ አንዳች ብንለምን ይሰማናል። የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን።» 1ኛ የዮሐንስ መልእክት 5:14-15 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

80 «ሰለዚህ እላችኋለሁ፥ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፥ ይሆንላችሁማል።» የማርቆስ ወንጌል 11:24 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና።» ወደ ዕብራውያን 11:6 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

81 «...አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል። እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።» የዮሐንስ ወንጌል 16:23-24 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)። «እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ፥ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ሰም አድርጉት።» ወደ ቆላስይስ ሰዎች 3:17 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

82 «ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ። ለእርሱ አሁንም እስከ ዘላለምም ቀን ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።» 2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 3:18 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

83 «እግዚአብሔር ለሰጠው የተስፋ ቃል ሁሉ አዎን ማለት በእርሱ ነውና፥ ሰለዚህ ለእግዚአብሔር ሰለ ክብሩ በእኛ የሚነገረው አሜን በእርሱ ደግሞ ነው።» 2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1:20 (የ1954 ዓ.ም. ትርጉም)።

Amharic Scripture quotations: copyright © 1962, 2003 United Bible Societies. Revised Amharic Bible in XML (2003). Printed version by United Bible Societies (C)1962. E-Text in transliterated ASCII format by Lapsley/Brooks Foundation 1994. Unicode UTF-8 transformation and XML-tagging by Dirk Röckmann 2003 (www.nt-text.net). With kind permission of the Bible Society of Ethiopia. Every non-commercial work using this data in any form must fully include this copyright statement! Every commercial use of parts or the complete data in any form needs written permission of the Bible Society of Ethiopia!